የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ክ/መ/ቁ 285907

ልደታ ምድብ 9ኛ ገቢዎችና ጉምሩክ ወንጀል ችሎት ጥቅምት 02/2014 ዓ.ም

ዳኛ- መሰለ ንጉሴ

ከሳሽ - የፌ/ዐ/ህግ

ተከሳሽ- ወ/ሮ ማህሌት ተፈራ ገብረወልድ

መዝገቡ የተቀጠረው ፍርድ ለመስጠት ሲሆን ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍርድ</u>

ለዚህ ፍርድ መነሻ የሆነው ከሳሽ ዐ/ህግ በቀን 12/12/2012 ዓ/ም ፅፎ ያቀረበው የወንጀል ክስ ሲሆን ይዘቱም ተከሳሽ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀፅ 168/1 በአዋጅ ቁጥር 1160/2011 አንቀፅ 44/1 እንደተሻሻለው፤ የብሄራዊ ባንክ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 591/2000 አንቀፅ 20/2፤ የኢትዮጲያ ብሄራዊ ባንክ ማንኛውም ግለሰብ ከውጪ ሀገር ሲገባ ወይም ከሀገር ሲወጣ መያዝ የሚችለውን የኢትዮጲያ ብር ወይም የውጪ ምንዛሬ አስመልክቶ ያወጣው መመሪያ ቁጥር FXD/49/2017 አንቀፅ 4.1/ሀ በመተላለፍ እያወቀች ወይም ማወቅ ሲገባት በቀን 04/09/2012 ዓ/ም በግምት ከጠዋቱ 1፡35 ሰዓት አካባቢ በኢትዮጲያ አየር መንገድ በበረራ አስተናጋጅነት ስትሰራ ከቆየችበት ከአሜሪካ ዋሽንግተን ዲሲ ተነስታ አዲስ አበባ ቦሌ አለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ተርሚናል አንድ የጉምሩክ መፈተሻ ቦታ ደርሳ የኤክስሬይ ፍተሻ ተደርጎላት ካለፈች በኋላ በግምት ከቀኑ 5፡30 ሰዓት አካባቢ ሰራተኞች እንዲያልፉ በማይፈቀድበት ቦታ ስታልፍ ተገኝታ አካላዊ ፍተሻ እንዲደረግሽ ተርሚናል ሁለት የገቢ መንገደኞች መግቢያ አካባቢ በሚገኘው መጸዳጃ ቤት ውስጥ ገብታ በጥበቃ ሰራተኛ ስትፈተሽ በለበሰችው የውስጥ ሱሪ እና የሴቶች የንፅህና መጠበቂያ መካከል የአሜሪካን ዶላር የተገኘ ሲሆን ይህንን ተከትሎ ፍተሻውን ያከናወኑ የጥበቃ ሰራተኞች ከመጸዳጃ ቤቱ ከወጡ በኋላ የጉምሩክ ኦፊሰሮች በቦታው መጥተው ተከሳሽ ምን እንደያዘች ስትጠየቅ 300 የአሜሪካን ዶላር ብቻ እንደያዘች ያሳየች ቢሆንም የጉምሩክ ሰራተኞች መጸዳጃ ቤቱ ውስጥ ገብተው ፍተሻ ሲያደርጉ በመጸዳጃ ቤቱ ግድግዳ ላይ ባለው ሶፍት ማስቀመጫ ውስጥ ቀሪ ዶላሩን አስቀምጣው የተገኘ ሲሆን በአጠቃላይ

የተያዘው ገንዘብም ሲቆጠር 22,200 የአሜሪካን ዶላር በመሆኑ ተከሳሽ ምንም አይነት የጉምሩክ ስነ-ስርዓት ያልተፈጸመበት የውጪ ሀገር ገንዘብ በድብቅ ወደ ሀገር ውስጥ ልታስገባ ስትል በመያዟ በፈጸመችው የኮንትሮባንድ ወንጀል ተከሳለች የሚል ሲሆን ከክሱ ጋር የሰው ምስክሮች ስም ዝርዝር ከሰነድ ማስረጃ ጋር አያይዘው አቅርበዋል፡፡

የዐ/ህግ ክስና ማስረጃ ለተከሳሽ መድረሱ በችሎት ተረጋግጦ እና ክሱ በችሎት ተነቦ ተከሳሽ እንድትረዳው ከተደረገ በኋላ መቃወሚያ እንዳላት ተጠይቃ አለኝ በማለት ያቀረበች ሲሆን ፍ/ቤቱ በቀን 29/03/2013 ዓ/ም በብይን ውድቅ አድርጎታል፡፡ በመቀጠልም ፍ/ቤቱ የተከሳሽን የእምነት-ክህደት ቃል የተቀበለ ሲሆን ተከሳሽም ድርጊቱን አልፈጸምኩም ጥፋተኛም ልባል አይገባም በማለት ክዳ በመከራከሯ ፍ/ቤቱ በቀን 15/08/2013 ዓ/ም በዋለዉ ችሎት 5(አምስት) የዐ/ህግ ምስክሮች ተሰምተዋል፡፡

ሰይፈዲን ቁፋ የተባለው የዐ/ህግ ምስክር ቦሌ ኤርፖርት ውስጥ ፍተሻ ሰራተኛ መሆኑን በመግለፅ በቀን 04/09/2012 ዓ/ም ከቀኑ 5፡30 ሰዓት አካባቢ ተከሳሽ ሰራተኛ መውጣት በሌለበት በር እየወጣች እንደነበር በተለየ መልኩ ስትራመድ የነበር በመሆኑ እንድትቆም እንደጠየቃት እና ፍቃደኛ ባለመሆን እንደሄደች፤ ሄዶም እንዳስቆማት እና እንደተፈተሸች፤ በፍተሻም ወቅት ገንዘብ እንደተገኘ እና ለሚመለከተው የጉምሩክ አካል አሳውቀው ሲቆጠር 22,200 የአሜሪካን ዶላር መሆኑን መስክሯል፡፡

2ኛ የዐ/ህግ ምስክር ገነት ወርቁ ቦሌ ኤርፖርት ውስጥ ፍተሻ ሰራተኛ መሆንዋን በመግለፅ በቀን 04/09/2012 ዓ/ም ከቀኑ 5፡30 ሰዓት አካባቢ ሰይፈዲን ቁፋ የተባለው የዐ/ህግ ምስክር ተከሳሽ አረማመድዋ ትክክል ስላልሆነ ትፈተሽ እንዳላት እና ለመፈተሽ እንደሄደች፤ ተከሳሽንም ግላዊነቷን ለመጠበቅ መፀዳጃ ቤት አስገብታ ፍተሻ በሚደረግበት ወቅት ከውስጥ ልብሷ ዶላር እንደተገኘ እና ልብሷን እንድትለብስ ዘወር እንዳለች ከፊሉን የቆሻሻ ማስቀመጫ ፍሬሽ ካን ውስጥ ጥላው በጉምሩክ ሰራተኞች ለቆጠራ ስትጠየቅ 300 የአሜሪካን ዶላር አውጥታ እንዳሳየች እና መልሰው ሲፈትሹ ሌላውን ፍሬሽ ካን ውስጥ እንደተገኘ የጉምሩክ ሰራተኞች ባሉበት ሲቆጠር 22,200 የአሜሪካን ዶላር እንደሆነ መስክራለች፡፡

3ኛ የዐ/ህግ ሂላሪ አዲሱ የጉምሩክ ድንገተኛ ፈታሽ መሆንዋን በመግለፅ በቀን 04/09/2012 ዓ/ም ከቀኑ 5፡30 አካባቢ ላይ የኤርፖርት ሴኩዩሪቲ ባለሙያዎች እንደጠሩዋቸው እና ተከሳሽ መፀዳጃ ቤት ውስጥ እንደነበረች እና የውጪ ገንዘብ እንደያዘች እንደነገሯት እና ተከሳሽ 300 ዶላር ብቻ እንደያዘች እንደነገረቻቸው እና ከሰውነቷ ውስጥ አውጥታ እንደሰጠቻቸው፤ ሌላውን ደግሞ መፀዳጃ ቤቱ ውስጥ የሶፍት ማስቀመጫ ላይ አስቀምጣው እንዳገኙት መስክራለች፡፡

4ኛ የዐ/ህግ ምስክር ልዩ ላቀው የጉምሩክ ድንገተኛ ፈታሽ መሆንዋን በመግለፅ በቀን 04/09/2012 ዓ/ም ከቀኑ 5፡30 አካባቢ ከ3ኛ የዐ/ህግ ምስክር ጋር የኤርፖርት ሴኩዩሪቲ ባለሙያዎች በጠሩዋቸው መሰረት እንደሄደች እና ተከሳሽ ላይ ፍተሻ እንዳከናወነች፤ በፍተሻውም በተከሳሽ የውስጥ ልብስ ውስጥ 300 የአሜሪካን ዶላር እና የተቀረው ደግሞ በሶፍት ማስቀመጫ ውስጥ እንደተገኘ በአጠቃላይ 22,200 የአሜሪካን ዶላር እንዳገኙ እና ተከሳሽም ሰው ያዥልኝ ብሎኝ ነው እንዳለቻቸው መስክራለች፡፡

5ኛ የዐ/ህግ ምስክር እፋ መርጋ የጉምሩክ ዕቃ ፍተሻ ባለሙያ መሆኑን በመግለፅ በቀን 04/09/2012 ዓ/ም ከቀኑ 5፡30 አካባቢ ዶላር ተይዟል ተብሎ አንደተጠራ እና በወቅቱ ከተከሳሽ ላይ 22,200 የአሜሪካን ዶላር እንደተገኘ እና ቆጥሮ ለባንክ እንዳስገባው እና ተከሳሽንም ወደ ምርመራ ክፍል እንደወሰደ መስክሯል፡፡

በዐ/ህግ የሰነድ ማስረጃ 1ኛ) የተከሳሽ ፓስፖርት 01 ገጽ ኮፒ፤ 2ኛ) 22,200 የአሜሪካን ዶላር የተመዘገበበት ቁጥሩ 008035 የሆነ ዲክላራሲዮን እና በተከሳሽ የተፈረመ ሰነድ 01 ገጽ ኮፒ፤ 3ኛ) ከኢትዮጲያ አየር መንገድ በቀን 24/09/2012 ዓ/ም በቁ.አአመ/8/ሕ/4991/12 ተከሳሽ የድርጅቱ ሰራተኛ መሆኗን፣ በ04/09/2012 ስራ ላይ የነበረች መሆኑን እንዲሁም የስራ መዘርዘርሩን የሚገልፅ ሰነድ ከነትርጉሙ 08 ገጽ ኮፒ፤ 4ኛ) በአ.አ ኤርፖርት ጉምሩክ ቅ/ፅ/ቤት በቀን 13/11/2012 በቁጥር 08/07/538/2012 የተጻፈ ከተከሳሽ የተያዘው ገንዘብ ዲክሌር ያላደረገች መሆኑን የገለጸበት ሰነድ 01 ገጽ ኮፒ፤ 5ኛ) በክሱ የተቀሰው ዕቃ ባንክ ገቢ የተደረገበት ደረሰኝ ከነትርጉሙ 02 ገጽ ኮፒ ማስረጃዎች ተያይዘው ቀርበዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የዐ/ህግን የሰው እና የሰነድ ማስረጃ መርምሮ የዐ/ህግ የሰው እና የሰነድ ማስረጃ በክሱ በዝርዝር እንደተጠቀሰው ተከሳሽ በቀን 04/09/2012 ዓ/ም በግምት ቀኑ 5፡30 ሰዓት አካባቢ በቦሌ አየር መንገድ ውስጥ ገደብ የደረገበትን እና የጉምሩክ ስነ ስርዓት ያልተፈጸመበትን 22,200 የአሜሪካን ዶላር ይዛ መገኘትዋን በበቂ ሁኔታ የሚያስረዳ መሆኑን፣ ክስ የቀረበበት የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 168/1 ማሻሻያ አዋጅ 1160/2011 አንቀፅ 44 እንደተሻሻለው ድንጋጌም ማንም ሰው እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባው የጉምሩክ ህጎችን በመተላለፍ የተከለከለ፣ ገደብ የተደረገበት ወይም የጉምሩክ ስነ-ስርዓት ያልተፈጸመባቸው ዕቃዎችን ከጉምሩክ ክልል ያስገባ ወይም ከጉምሩክ ክልል ከሀገር ያስወጣ ወይም ለማስወጣት ወይም ለማስገባት የሞከረ እንደሆነ የዕቃው መወረስ እንደተጠበቀ ሆኖ ድርጊቱ በወንጀል እንደሚያስጠይቅ የሚደነግግ መሆኑን፣ የብሔራዊ ባንክን ለማቋቋም የወጣውን አዋጅ ቁጥር 591/2000 አንቀጽ 20/2/ ኢትዮጲያ ውስጥ ነዋሪ

የሆኑ፣ ነዋሪ ያልሆኑና ለጉብኝት የመጡ ሰዎች ወይም ሌላ ማንኛውም የውጭ ምንዛሬ የሚይዝበትን ወይም ክፍያ ማዘዣዎችን የሚይዝበትንና የሚጠቀምበትን ሁኔታዎችና ገደቦች ብሄራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን መሆኑን እንደሚያስቀምጥ እና በብሄራዊ ባንክ የወጣው መመሪያ ቁጥር 49/2017 አንቀፅ 3.1 ደግሞ ከ1000 ዶላር በላይ ይዞ ወደ አገር ውስጥ የሚገባ ሰው ዲክሌር ማድረግ እንዳለበት የሚያስቀምጥ መሆኑን እና ተከሳሽም በህግ ገደብ የተደረገበትን እና ሰነድ ያላቀረበችበትን የውጭ ሀገር ገንዘብ ይዛ መገኘቷን ዐ/ህግ በበቂ ሁኔታ ባቀረበው ማስረጃ ስላረጋገጠ ተከሳሽ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀፅ 168/1 በአዋጅ ቁጥር 1160/2011 አንቀፅ 44/1 እንደተሻሻለው የተመለከተውን በመተላለፍ የቀረበባትን የኮንትሮባንድ ወንጀል እንድትከላከል በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ ቁጥር 142 መሰረት ብይን ተሰጥቷል።

ተከሳሽ ትከላከል ከተባለ በኋላ የምታቀርበው መከላከያ ማስረጃ እንዳለ ተጠይቃ አለኝ በማለት በቀን 19/11/2013 ዓ/ም ሁለት(2) መከላከያ ምስክሮችን አቅርባ አሰምታለች። እንዲሁም 01 ገፅ የሰነድ ማስረጃ አቅርባለች፤ የተከሳሽነት ቃሏንም ሰጥታለች።

ተከሳሽ በሰጠችው የተከሳሽነት ቃል የኢትዮጲያ አየር መንገድ በረራ አስተናጋጅ ሰራተኛ መሆንዋን፣ በአብዛኛው በረራ የምታደርገው አሜሪካን እና ካናዳ ሀገር እንደሆነ፤ ከደሞዝዋ ውጪ የውሎ አበል ዶላር እንደሚከፈላት እና መኪና መግዛት ስለምትፈልግ ዶላሩን ቤትዋ ውስጥ እንደምታጠራቅም፤ በቀን 04/09/2012 ዓ/ም ከአሜሪካ እንደተመለሰች እና ባለቤትዋ መኪና እንደምትገዛ ስለማያውቅ እሱን ሰፕራይዝ ለማድረግ በማሰብ ደላሎችን መኪና እንዲገዙላት ነግራቸው እንደነበር እና መኪና እንደተገኘላት እንደነገሩዋት ከዛም ባለቤትዋ መጥቶ ከአየር መንገድ እንደወሰዳት እና ቤት ሄዳ ዩኒፎርሚን ሳትቀይር ይጠራቀመችውን ዶላር ይዛ እንደወጣች፤ ሄዳም መኪናውን ስትመለከት አሮጌ እና ዋጋውም ከፍ ያለ ስለነበር ሳትገዛው ወደ አየር መንገድ እንደተመለሰች፤ በአየር መንገዱ ህግ መሰረት ብር የዩኒፎርም እስቶኪንግ ውስጥ ገንዘብ እንደሚያስቀምጡ እና እሱዋው የዛን ቀን ብሩዋን እዛ ውስጥ አድርጋ እንደነበር፤ ወደ አየር መንገዱ ተርሚናል ሁለት ውስጥ ልትገባ ስትል በሚደረገው ማስፋፊያ ኮንስትራክሽን መሰረት ስላላወቀችው መግቢያውን ሰው ጠይቃ እንደገባች እና ስትገባም ማንም ሰው እንዳልጠየቃት፤ የያዘችው ዕቃ ምግብ ነክ ስለነበር እቃው የሚቀረጠው ተርሚናል ሁለት ስለነበር እዛ እንደሄደች፤ ከዛም ዕቃውን አጥሩቭ አስደርጋ ጉምሩክ ደግሞ ዋጋውን አስተምና ከፍላ ዕቃውን ከተርሚናል አንድ ለማውጣት በምትወጣበት ጊዜ 1ኛ ዐ/ህግ ምስክር የነበረውን መውጣት ይቻላል ወይ ስትለው አዎ ብሎ በእጁ ምልክት እንደሰጣት እና በመውጣት ላይ እያለች የፌደራል ፖሊስ ልብስ የለበሰ ሰው

እንዴት ሳትፈተሺ ትገቢያለሽ ብሎ ግርግር እንደተፈጠረ፤ ብሩን ሊቀሙኝ ነው በማለት በማሰብ ካስቀመጠችበት ቦታ ዞር በማድረግ እንደደበቀችው፤ ሲሲቲቪ ላይ ይታይልኝ በዚሁ ነው የገባሁት በማለት እንደታየ እና የገባችው በዛ በር መሆኑ እንደታየ፤ በገባችበት ስለወጣች ትፈተሺ ተብሎ እንደተፈተሸች እና ለፈታሸዋ ገንዘብ እንደያዘች እንደነገረቻት እና ቦታውን ነግራት ወደ ሽንት ቤት ወስዳ እንደፈተሸቻት እና ገንዘቡም እንደተገኘ እና ገንዘቡንም እንደሰዱት ገልጻለች፡፡

1ኛ መከላከያ ምስክር አለም ሞገስ የኤርፖርት ጉምሩክ ቅርንጫፍ ፈታሽ መሆንዋን በመግለፅ በቀን 04/09/2012 ዓ/ም በግምት ከጠዋቱ 1፡35 አካባቢ ተከሳሽ የበረራ አስተናጋጅ ሆና ከአሜሪካን እንደመጣች እና ተርሚናል አንድ ውስጥ በኤክስሬይ ማሽን ፍተሻ ተደርጎላት እንዳለፈች ከዛም ኤክስሬይማኑ ማስቲካ እንደያዘች እንደነገራት እና ፈትሻ ያገኘችውን ማስቲካ ቀረጥ እንድትከፍል በጉምሩክ ዲክላራሲዮን ፅፋ እንደሰጠቻት እና ከዛ በኋላ ወዴት እንደሄደች እንደማታውቅ መስክራለች፡፡

2ኛ መከለከያ ምስክር አብነት ደምሳ የተከሳሽ ባለቤት መሆኑን በመግለፅ በቀን 04/09/2012 ዓ/ም ተከሳሽ ስትገባ በሰላም እንደገባች እንደምትደውልልለት እና የዛን ቀንም እንደደረሰች ስትደውልለት ከጓደኛው መኪና ተቀብሎ ወደ ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት አካባቢ አየር መንገድ ሄዶ እሷን እና ሻንጣዋን ይዞ ወደ ቤት አድርሷት እሱ ወደ ስራ እንደሄደ መስክሯል፡፡

የሰነድ ማስረጃን በተመለከተ የወንጀል ድርጊቱ ተፈጸመ በተባለ ቀን ተከሳሽ ማስቲካ ይዛ እንደገባች እና ቀረጥና ታክስ እንዲከፈልበት ያሳወቀችበትን 01 ገጽ ኮፒ አያይዛለች፡፡

ፍርድ ቤቱም ተከሳሽ የቀረበባትን ክስ ተከላክላለች? ወይስ አልተከላከለም? ጥፋተኛ ልትባል ይገባል? ወይስ አይገባም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ መዝገቡን አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች አንጻር እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ተከሳሽ ያቀረበችውን መከላከያ ማስረጃ ከዐ/ህግ ማስረጃ ጋር አጣምረን ስንመለከት የዐ/ህግ ምስክሮች እና የሰነድ ማስረጃ ተከሳሽ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ሰራተኛ መሆኗን፣ በ04/09/2012 ዓ.ም ከአሜሪካ በረራ አድርጋ ወደ ኢትዮጵያ እንደገባች፣ ከቀኑ 5፡30 አካባቢ የአየር መንገዱ ሰራተኞች በማይወጡበት በር በኩል የሰራተኛ ልብስ ለብሳ ስትወጣ እንድትቆም ተጠይቃ ስትፈተሽ በክሱ የተጠቀሰው ዶላር መገኘቱን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ የተከሳሽ ምስክሮች ቃል ደግሞ ተከሳሽ በእለቱ ከአሜሪካን በረራ በማድረግ ከጠዋቱ 1፡35 ሰዓት እንደገባች እና ተርሚናል አንድ ቀጥታ ወደ ፍተሻ እንደመጣች እና በፍተሻም ወቅት ማስቲካ ይዛ እንደነበር እና ቀረጥ ማስቀረጫ ዲክላራሲዮን እንደተሰጣት፣ ከበረራ ስትገባ

ዕቃዋን ይዛ ወደ ቤት እንደሄደች የሚገልፅ ነው፡፡ የዐ/ህግ ማስረጃ ተከሳሽ በእለቱ ከአሜሪካ ወደ ኢትዮጵያ እንደገባች እና ከቀኑ 5፡30 አካባቢ ከአየር መንገዱ መውጫ በር ላይ ልትወጣ ስትል በተደረገ ፍተሻ ዶላሩ እንደተገኘ የሚያረጋግጥ ሲሆን የተከሳሽ ምስክሮች ተከሳሽ በእለቱ 1፡35 አካባቢ በአየር መንገዱ ደርሳ ፍተሻ ተደርጎ ለማስቲካ የቀረጥ ማስከፈያ ዲክላራሲዮን እንደተሰጣት የሚያሲረዳ ቢሆንም ተከሳሽ በእለቱ ይዛው የተገኘችውን 22,22 የአሜሪካ ዶላር ከውጪ አገር ይዛው የገባችው ስላለመሆኑ፣ ወይም በህጉ መሰረት ዲክሌር አድርጋ የገባች ስለመሆኑ፣ ወይም ከሌላ የአገር ውስጥ ህጋዊ ምንጪ ያገኘችው ወይም ህጋዊ ሰነድ ያለው ስለመሆኑ የሚያስረዳ አይደለም፡፡ ተከሳሽ ዶላሩን ከቤቱ መጥቼ ተመልሼ ይገርው ወደአየር መንገዱ የሔድኩት ነው በማለት የሰጠችው የተከሳሽነት ቃልም በሌላ ገለልተኛ ማስረጃ የተደገፈ አይደለም፡፡ ከቤቷ የወሰደችው ቢሆን እንኳን በህጋዊ መንገድ አሳውቃ ወደ አገር ውስጥ ያስገባችው ወይም ህጋዊ የባንክ ሰነድ ያለው ስለመሆኑ ያቀረበችው ማስረጃ የለም፡፡

በአጠቃላይ ተከሳሽ በእለቱ ከአሜሪካ በረራ አድርጋ ወደ ኢትዮጵያ አየር መንደገድ እንደገባች እና ከቀኑ 5፡30 አካባቢ ፍተሻ ሲደረግ ዶላሩን ይዛ እንደተገኘች በዐ/ህግ ማስረጃ በበቂ ሁኔታ የተረጋገጠ በመሆኑ እና የተከሳሽ መከላከያ ማስረጃ ተከሳሽ ዶላሩን በእለቱ ከውጪ አገር ይዛው እንዳልገባች ወይም ያሳወቀችው ወይም ህጋዊ ሰነድ ያለው ስለመሆኑ የሚያስረዳ ስላልሆነ እንድትከላከል የተባለውን የኮንትሮባንድ ወንጀል በአግባቡ ተከላክላለች ለማለት አልተቻለም፡፡ ስለሆነም የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 168/1 ማሻሻያ አዋጅ 1160/2011 አንቀፅ 44(1) በመተላለፍ የተከሰሰችበትን የኮንትሮባንድ ወንጀል የፈፀመች ጥፋተኛ ናት ተብሎ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 149 መሰረት የጥፋተኝነት ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

በመቀጠልም ፍ/ቤቱ የቅጣት አስተያየት እንደሚከተለው ተቀብሏል፡፡